# ጀግናዬ

www.yehaarts.com

ታደለ አያሌው
+251(0)912944937
አዲስ አበባ

- ፩ -

**ውጭ -- ሠማይ ጠቀስ ተራራ ግርጌ -- ምሽት፣ ጳጉሜን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.**

*/ፈርጠም ያለ ጎበዝ፣ ሽፍታ መሳይ ባለጎፈሬ፣ እረኛ መሳይ ባለዋሽንት፣ ንጉሥ መሳይ ኩሩ፣ ወታደር መሳይ ወኒያም ቆፍጣና። ከላይ ያደፈ ሸማ ሹራብ፣ ከታች ያጠረ ቁምጣ አድርጎ፤ ዋሽንቱን ልብ በሚያስከዳ ዜማ ካፉ ለግቦ እጅግ ከፍ ካለ ተራራ አናት - ዓለምን ከዳር እስከ ዳር ሊያሳይ በሚያስችል ጉብታ ጫፍ ሆኖ ይቃብዛል። ...ቁልቁል - ምልሰት፡፡/*

LAP DISSOLVE

- ፪ -

- **ምልሰት** -

**ውጭ -- ትልቅ ዋርካ ስር -- ጠዋት፣ መስከረም ፲፱፻፳፱ ዓ.ም.**

*/አንድ ልጅ እግር፤ እያንጎራጎረ ቀጥ ያለውን ዋርካ ሊወጣ ይወድቅ ይነሳል። እንደምንም ከፍ ሲል የያዘው ቅርፊት አምልጦት ወደቀ። ደግሞ ፋጭሮ ተቃና። ... ከዋርካው አናት፣ ሠማዩ ላይ ቀስተ ደመናው ኂ! ብሎ ተነጥፏል - የኢትዮጵያ አርማ!... በእረኞች ‹አዋዎ› ዜማ ጉሮሮውን እየጠነቆለ... ።/*

**ህጻን(OS.)፡**-አዎዋ... አለያ... ለያ! ለያ! ለዋ! አዎዋ... አለያ... ለያ! ለያ! ለዋ!
ከሠማይም ሽቅብ -አዎዋ! ሠማይ አለ እላለሁ፤ -ዎአ!
ከምድርም ቁልቁል -አዎዋ! ምድር አለ እላለሁ፤ -ዎአ!
ኢትዮጵያን የሚያህል -አዎዋ! የለም ስል አምናለሁ። -ዎአ!
አዎዋ... አለያ... ለያ! ለያ! ለዋ! አዎዋ... አለያ... ለያ! ለያ! ለዋ! ...

LAP DISSOLVE

- ፫ -

**ውጭ -- ሠማይ ጠቀስ ተራራ ግርጌ -- ምሽት፣ ጳጉሜን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.**

*/ሽቅብ - ከምልሰት መልስ፡፡ ሠማዩንና በሠማይ ያለውን ቀስተ ደመና ሽቅብ በጥሞና እያየ ...። እያደር ቁልቁል አንገቱን ሲሰብር የተዝጎረጎረ ወጣ ገባ መሬት - የኢትዮጵያ መልክአ ምድር ነው። ኢትዮጵያን በለዘበ ወግ ያወጋት ጀመር።/*

**ጆቴ፡-** አይገርምሽም?
ለካንስ ፈጣሪዬ - እግዜርሽ
እሚያመነጭ - እሚያነጥፍሽ፣
ወይ እሚያስብል - ወይ እሚልሽ፤
በዚህ ብጤ ተራራ አናት በኔን መሳይ ጥሞና
ሲታዘብሽ ባጅቷልና ...
ጉድ እኮ ነው ጱንጥ!
ለካንስ፤ ከእንዲህ ያለ ጉብታ ጣራ የእግዜር ያህል ካስተዋሉ፣
ኢዛናና ሳይዛና ያኮራሉ።
እነ ያሬድ ይሠማሉ።
አበበና ሮም ይታያሉ።

ተራራ ካሉስ ዕልቅና ...

*/በየመሃሉ ነገረ አንጀቱን በዋሽንቲ ዋይታ እየተነፈሠ ... አፍታ ጊዜ ወደ ሮም - ጣሊያን አሻግሮ ቢያይ፤ እጅብ ብለው ከሚባክኑት ጥቁርና ነጭ ሯጮች ጋር አበበ ቢቂላ ያውም በባዶ እግሩ በልበ ሙሉነት እየገሠገሠ ነው፡፡/*

**ጆቴ፡-** አላልኩሽም?



www.yehaarts.com

የጥቁር ወኔ እንዲግል የነጭ ልብ እንዲማልል
ምድረ ሮም፣ በአበበ ቢቂላ ተወሯል።
ሩጥልኝማ ጀግናዬ ...
እና፤ በባዶ እግሩ ከልማድ በስቲያ ከብርቱዎች ጋር የተናነቀው፣
የ‹አንተ ታንስ›ን ድንበር ሊንድ በጥንተ ነገርሽ ቢታበት ነው።
ጉድ እኮ ነው ምድረ አጋዝያን!
ከነገደ ኩሽ ውብ ወዶ የዮቅጣን ጉርባ ሲነሆልል
ከሴም ዘር ኀበዝ ፈቅዳ የኩሽ ጉብል ስታባብል፣
ዘር ከዘር ልብ ለልብ ተፈቃቅደው
የተዋጉ ነገዶች በጋብቻ ይቅር ብለው፤
ሲታዩት ይታየኛል፣ ሲጠበቡ ከድንጋይ ጋር ሲሟገቱ
ሃሳብ ከሃሳብ እያፋጩ በፍልስፍና ሲዋትቱ፤
ከማዶ ማዶ የነጋዴን፣ ከግዛት ግዛት በየልፍኙ፣ ንጉስ በጠና ሲያማልሉ
ያቢሲኒያን ስም እያጓኑ፣  የሁሉ መገኛዎች፣ የለከት ልክ ሲባሉ፤
ወርቅ አቅልጠው፣ ብራና ዳምጠው፣ ቀለም በጥብጠው፣
ቅጠል ቦጭቀው፣ ቀንድ አለስልሠው፣ ማዕድ ሞልተው...

ሲሰሙት...

ይሠማኛል ሲሸልሉ
በአንድነት ዘራፍ ሲሉ።
ዘራፍ! አካኪ ዘራፍ!!
የንጉሥ ሎሌ ያባ ከበርቴው
የካሌብ አሽከር በውሃ እሚሮጠው፤
ገፍቶ ከመጣ ‹ተው› ካተልሠማው...
ሳገላብጠው፤ ከል ሳለብሠው፣
ስከነችረው፤ እዥ ሳስነባው፣
ይኸው ነኝ እኔ እጄን ይቅመሠው!!
እትትትትትትት ....!!! ...
ውል ይሉኛል ባይኑ ሲዞሩ ባይኔ ይዞሩ፣ ...
ወኔ ተሻምተው ባንድ ሲያብሩ።

*/አበበ ቢቂላ፤ የሞሮኮውን ራሀዲ ቤን አብዴ ሰላም እና የኒውዚላንዱን ባሪ ማጊ አስከትሎ በመሮጥ ላይ መሆኑን አይቶ ይልቁን ጋለ።/*

**ጀቴ፡-** ኧረ እይውማ... ቀደመ! አዎ አበበ ቢቂላ ከፊት እየተፈተለከ ነው፡፡ ድፍን አፍሪካ ሊነቃነቅ፣ አዳሜ ሁሉ ጉድ ሊል... አበበ ቢቂላ!! ጥቁሩ አፍሪካዊ! በባዶ እግሩ!!
ገስግስ ጀግናዬ!
ቀድመህ ልይህ ብርቱዬ! ...
ቻለውማ እንዲያ መኩሪያዬ!
አዎ እየመራ ነው!!

ተራራስ ካሉ ልዕልና ...
እና፤ ቀድሞውንም ከቀለም በስቲያ ከዘረኞች ጋር መተናነቁ፣
ተከተሉኝ ለማለት ነው ጥንተ ነገርሽን ያላወቁ እንዲያውቁ።
አጀብ እኮ ነው ምድረ ሃበሻ!



www.yehaarts.com

ጉብታ አናት ጉብ ብለው አሻግረው ልብ ካሉ
ሶሐባዎች ይሠማሉ።
‹ሃበሻ የእምነት ምድር - የሃቅ የሠላም ቦታ፣
ነጃሺ ድንቅ ንጉሥ - የሃበሻ በፍቅር ጌታ፣
ህዝቦቿ እንግዳ ወዳጅ - የነጃሺ ቅን ሥጦታ›፣
እያሉ በመንዙማ በረሃውን ሲያቋርጡ፣
ሲታዩት ...
ይታየኛል እኒውልሽ እልል እያሉ ሲመጡ።

እያደር ልዕልናሽ ሲደራ ግርማሽ ከጽንፍ ጽንፍ ሲወሳ፣
እያደር ክንድሽ ሲፈረጥም ግርሻ ግሥላ ልጅሽ ሲያገሳ፣
እያደር ባድማሽ ሲቀልዝ የረመጥ ላንቃ ልጆችሽ ሲግሙ፣
እያደር እንብላሽ ያሉ ከጨፍጨፊ ጨፍ ሲሉ ሲከስሙ፣
ገብረ መስቀል በያሬድ ዕልቅና በስሜት ሲናውዝ፣
ለአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ሥነ ጽሑፍ ስትታዘዝ፣
ላሊበላ ከነህዝቡ ከድንጋይ ቤት ሲያዋቅሩ፣
አባ ታጠቅ - አባ ጃሂድ - አባ በዝብዝ - አባ ዳኛው - አባ ጤና - አባ ጠቅል - ሲያጣብኑ ሲጥሩ፤
አንድ አይነት ጅራፍ የገረፈን፣ በእኩል ሠሞን ቡቃችን የነጠፈ፣ በአንድ አይነት ሠይጣን የተፈተንን፣
ያንዳችን ቡግንጅ ሁላችንን ያሳከከን፣
በአንዲቷ ኢትዮጵያ የባጀን!

ተራራ ቢሉስ ፍቅር ...

*/ረዥም ፋታ - ጥሞና። በአርምሞና በተመስጦ ሠማይ ላይ ከደመናው መሳ ለመሳ የኅላውን የኢትዮጵያን አርማ ከበታቹ ከጸናው መልክዐ ምድር ጋር እያስተያየ። ... /*

**ጆቴ፡-** ኅራው ና ... ኅራው ና ... ኅራው ና ...
ናልኝ ሆድ አንጀቴ...
እናቴን እናቴን፣ እናቴን ይላሉ ምን እናት አላቸው
ታዲያን ከሠው እናት ምኑ ለገባቸው!?
የጀግናዬን እናት ለምን ይነኳታል፣ የጀግኖችን እናት ለምን ይነኳታል?
ለምን ያስቱኛል ካሠርቱ እንዳጎድል...
ባገሬ ተሣልቀው እተኛ ይመስል። ኅራው ና ...

ለካንስ ፈጣሪዬ እግዜርሽ
ትሁነኝ ብሎ ያበጃጀሽ ...

ብረርልኝ ኧረ እንዲያ አቤ፣ ጀግናዬ!
ኧረ ቅደምልኝማ እንዲህ አቤ፣ መኩሪያዬ!
እንዲያውም ከዚህ ጸንቶ ቢያደምጡ የፈጣሪን ቃል
ከነበረን ጸጋ ይልቅ የሚኖረን ይረቃል።
ከኖርነው ዕድሜ ይልቅ የምንኖረው ያጓጓል።
እና፤  ባንድነት ስናሟጥጥ ነፍስ ለነፍስ ስንግባባ
ባንድ ውለን ከተፈጠምን ነፋስ በመሃል ካልገባ፤
ተማምለን ከፏጨርን፣ ተፍጨርጭረን ከሮጥን፣ በመንደርደር ከጸናን፣ ከፈጣሪ ከተማጠንን፣
ማን ሊያግደን!?



www.yehaarts.com

*/ወዲያው ወደ ሮም ቢዞር፣ ሞሮኮዊው ራሀዲ አበበን ሊቀድም ጥርሱን ነክሶ እግር በእግር ይባክናል። ... ድንጋጤ .../*

**ጀቴ፡-** ወይኔ ጉዴ! ኧረ ጉዴ! አቤዋ? ... ኧረ እንዳይቀድምህ! ኧረ ...
ጉድ በል ህዝበ ሐበሻ!?
ልንሸነፍ?!!

*/ተሥፋ ለመቁረጥ የተቃረበ ልዝብ ልሳን።/*

መቼ ነው ግን እክል ያገኘሽ?
እኔ እያለሁ? እኔው ለኔ ብሼ?
ኧረ እኔስ አልቅስ አልቅስ ብሎኛል፣ እንኳንስ እናትህ...
ላልቅስ እንዴ ልነፍርቅ?
እድፍ ጉድፍ ችግርሽ በእንባዬ ቢለቅ?
የተራቡት ይጠግቡ፣ የከፋቸው ይጽናናሉ? ... የሚበላሽ ይጠረቃ፣ የሚከዱት ያምናሉ? ... ያልበሠለው ይሠክን፣ የተኮነኑት ይጸድቃሉ?
እምቢ!! እሺ።
አበበ ቢቂላ!!! ... ይልቁን ቀደመ። አዎ!

*/አበበ ቢቂላ። ይልቁን ፍጥነት ጨምሮ ወደ ማብቂያው ሸመጠጠ። በታዳሚው ህዝብ የድጋፍ ጩኸት ታጅቦ የመጨረሻውን መጨረሻ አጣዳፈው። ... በባዶ እግሩ አሸነፈ! ጥቁሩ አፍሪካዊ! ለመጀመሪያ ጊዜ ቀደመ። ታዳሚው ሁላ ‹አጀብ› አለ። የኢትዮጵያ ሠንደቅ አላማ በሮም - ጣልያን አገር ተውለበለበ። ... አበበ ቢቂላ ከቀዳማዊ ዐጼ ኃ/ሥላሴ እጅ ተሸለመ።/*

ይበሉ ንጉሥ ሆይ፤ እግሩን ይጠቡልኝ።
ይበሉ አቡን ሆይ፤ እግሩን ያስሙልኝ።
ልዕልት ሆይ! ቅድስት ሆይ!...
ይኸው ቃል ለሠማይ ለምድር፣
  የልዕልናሽ ባጥ ሲሰቀል፤ ‹‹ከፍ አርግ! ወድር ወደሠማይ!!›› ሲባል እጇ ላይዝል፣
  የአንድነትሽ ማገር እንዳይበሽክ ቅጥ ባለው ፍቅር ለዝንታለሙ ላውል፤
ይኸው ቃል ለሠማይ ለምድር
  መሃሉ ባይነገርም፣
  ማየልሽ ግን አይቀርም።
ተራራስ ቢሉ **ኢትዮጵያዬ**!!!!

www.yehaarts.com